| | |
|---|---|
| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ<br>ኢየሱስ ክርስቶስ<br>ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ<br><u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u> | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር<br>ድንግል ማርያም<br>እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ<br><u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u> |
| The Conquering Lion of the Tribe of Judah<br>Jesus Christ<br>Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian<br>King of Zion and King of Kings of Ethiopia | Ethiopia stretches out Her Hands to God<br>The Virgin Mary<br>Mother of God and Our Holy Mother<br>Queen of Zion and Ethiopia |

ቍጥር ፫/፳፻፮ ዓ. ም.

# ቃለ ዐዋዲ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የአዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

**በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤**
**አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤**
**በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥ ወንግሥትነ፡**
**ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤**
**በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥ ወካህንነ፥ ወንጉሥነ**
**ኢየሱስ ክርስቶስ፡**
**ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።**

**+ + +**

# ይድረስ፡-

## ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት
## የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች!

**ስለግእዝ ምንነትና ማንነት፡** በሚበቃ አውቃችኋል።

ከዚህ እውቀታችሁ የተነሣ፡ በሰብአዊው ተፈጥሮአችን፡ የዘር ግንዳችን የኾኑት፡ አዳም እና ሔዋን፡ ከፈጣሪያቸውና ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር ያገኙትና እርሱ፡ ከእነርሱ፥ እነርሱም፡ ከእርሱ ጋር፥ እርስ በእርሳቸውም ይነጋገሩበት የነበረው፡ የመጀመሪያው የሰው ልጆች ቋንቋ፡ **ግእዝ** መኾኑን ተገንዝባችኋል።

ከዚህ ግንዛቤያችሁም የተነሣ፡ በፍጥረት የልደት ዘመን፡ "**ወአሐዱ ነገሩ፡ ለኵሉ ዓለም፤ ወአሐዱ ቃሉ።**" ማለትም፡ "**የሰው ኹሉ ቋንቋው አንድ፥ አነጋገሩም፡ አንድ ነበር።**" ተብሎ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቦ የሚዘከረው፡ ያ አንድ ቋንቋ፥ ያ አንድ ንግግር፡ **ግእዝ** መኾኑን፡ በእምነት ተቀብላችኋል።

ኖኅና ሚስቱ ሓይከል፥ ሦስቱ ልጆቻቸው፡ ሴም፥ ካም፥ ያፌት እና ሦስቱ ሚስቶቻቸው፡ ምድርን፡ ከጥፋቷና ከርኵሰቷ ሊያጸዳት ካጥለቀለቃት የውኃ ሙላት የዳኑባት መርከብ ባረፈችበት መሬት ላይ በማኅበረሰብነት መኖር ከጀመሩ በኋላ፡ ወልደውና በጋብቻ ተዋልደው፡ እየበዙ ከኼዱም በኋላ፡ ዓለሙን ተከፋፍለው እስከተበታተኑበት ጊዜ ድረስ፡ ይነጋገሩበት የነበረው ቋንቋቸው፡ ይኸው **ግእዝ** እንደነበረ አረጋግጣችኋል። (ዘፍጥ. ፲፩፥ ፩።)

*ዐምሓርኛ*፡ (በመካከለኛው *ምሥራቅ* አጠራሩ፡ "አራማይክ" የሚባለው)፡ በተመሳሳይ ትርጉሙ፡ "ነጻ ሕዝብ" ላስሰኘው፡ ለዐምሓራነት መለያ ቋንቋ እንደመኾኑ መጠን፡ እነዚያን፡ **የግእዝ** ተናጋሪዎቹን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ ከግእዝ ቋንቋቸው የተነሣ፡ "ራሳቸው ነጻ ኾነው፡ ሌላውንም፡ ነጻ የሚያወጡ ናቸው" በማሰኘት፡ "አግኣዝያን" ይባሉ እንደነበረ ይታወሳል።

ከዚህ የሚከተሉት ሰባት እውነታዎች፡ የግእዝን ምንነትና ማንነት፡ በአዎንታዊ መልኩ፡ በቀላሉና በግልጽ አስረግጠው፡ በአጽንዖት ያስረዳሉ፦

፩ኛ፡ የራሱ፡ የግእዝ ትርጉም፡ "መጀመሪያ" እና "ነጻ" ማለት መኾኑ፤

፪ኛ፡ በሰባት ብዛት የሚወሰን ቍጥር፡ መለኮታዊ ምሥጢር ያለበት መኾኑን በማስገንዘብ፡ እያንዳንዱ **የግእዝ** ፊደል ሆሄ፡ በስም፥ በመልክና በድምፅ ይዘቱ በተቀዳጃቸው፡ በሰባቱ ፍጹማን ባሕርያት ተለይቶ መታወቁ፤

፫ኛ፡ የእያንዳንዱ **የግእዝ** ፊደል አሌፋት፡ የመጀመሪያ ቅርጽ፡ አፍ ሳያስከፍት፡ ግዑዝ በኾነውና **"ግእዝ"** በተባለው፡ በተፈጥሮ ድምፅ ብቻ መነገሩ፤

፬ኛ፡ "አ(ኧ)" የሚለው፡ የፊደላችን አሌፋት መነሻ፡ **በግእዝ፡** "ፍጹም ያማረ" የሚል ትርጉም ባለው፡ **"አዳም"** በሚል ቃል፡ በወንድና በሴት ጾታዎች ለተገለጹት፡ ለመጀመሪያዎቹ ሕያዋን ፍጡሮች መገኛ ይኾን ዘንድ፡ በአንድ አካልነትና በአንድ ባሕርይነት፡ በእግዚአብሔር መልክ ለተፈጠረው ቀዳሚው ሰው መጠሪያ ኾኖ መሰጠቱ፤

፭ኛ፡ በመላው ዓለም ያሉ፡ ሌሎቹ የሰዎች ቋንቋዎችና ፊደሎቻቸው፡ በተናጋሪዎቻቸው ሕዝቦች፥ ወይም፡ ኀሣዎች ስሞች ሲጠሩ፡ **"ግእዝ"** ግን፡ በራሱ ስም ብቻ መጠራቱ፤

፮ኛ. በምድር ላይ የሚኖሩ የሰው ልጆች ኹሉ፡ ተወልደው፡ በሕፃንነታቸው፡ መናገር በሚጀምሩበት ጊዜ፡ ቋንቋዎቻቸውና ፊደሎቻቸው፡ የተለያዩ ሲኾኑ፡ አፋቸውን ለመፍታት፥ አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውንም ለይተው ለመጥራት፡ "አባባ!" እና "እማማ!" እያሉ የሚለማመዱባቸው፡ "አብ አብ አብ" እና "እም እም እም" የሚሉት ቃላት፡ በቀጥታ፡ "አባት አባት አባት"" "እናት እናት እናት" የሚል ፍቺ ያላቸው፡ ፍጹም **ግእዝ** መኾናቸው፤

፯ኛ. **ለግእዙ** ፊደላችን፡ መደበኞች የኾኑት ኻያ ኹለቱ አሌፋት፡ ቍጥራቸው፡ እግዚአብሔር፡ በስድስቱ ቀኖቹ፡ በሥራቸው በሃያ ኹለቱ መደበኞች ፍጥረታት ልክ መኾኑና ራሳቸው አሌፋቱ፡ እያንዳንዳቸው፡ የእግዚአብሔር መታወቂያ ስሞች መኾናቸው ብቻ ሳይኾን፡ በስያሜ፥ በመልክና በድምፅ ይዘታቸው፡ ከተቀዳጁት፡ ከመለኮታዊው ሰባትነታቸው ጋር፡ በ"አ" ጀምረው፡ በ"አ" የሚፈጽሙ በመኾናቸው፡

"አነ ውእቱ፡ አልፋ ወኦ! አነ ቀዳማዊ፥ ወአነ ደኃራዊ! ርእስ፥ ወማኅለቅት!" ማለትም፡ "በቃልነቴ፡ ለማንነቴ መገለጫ፡ መነሻ እንደኾነው፡ እንደ'አ' እና መዳረሻው እንደኾነው፡ እንደ'አ' አሌፋት፡ እኔ፡ ፊተኛው እና ኋለኛው፥ መጀመሪያው እና መጨረሻው ነኝ!" ብሎ፡ ኋላ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" በተባለበት መጠሪያው፡ ራሱን፡ በሰውነት የገለጸው እግዚአብሔር፡ በዚህ፡ **የግእዝ** ስሙ፡ ማንነቱ የታወቀበትና አምልኮቱ የሚፈጸምበት ቋንቋና ፊደል ኾኖ፡ በሕያውነት፡ እነሆ እስከዛሬና ወደፊትም፡ ለዘለዓለም እንዲቀጥል ማድረጉ ናቸው። (ራእ. ፳፪፥ ፲፫።)

እንግዴህ፡ **ስለግእዝ ምንነትና ማንነት፡** እግዚአብሔራዊው እውነታ ይህ ከኾነ፡ **ግእዝ፡** "የእኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የምንነታችንና የማንነታችን፡ እውነተኛ መታወቂያችንና መለያችን መኾኑ ታወቀ፤ ተረዳ፤ ተረጋገጠ!" ማለት ነው። ስለዚህም፡ ራሱ፡ በተፈጥሮ ባሕርዩ፡ ሕያው ሲኾን፡ በእኛም፡ በእያንዳንዳችን አካላዊ ሕያውነት፡ እርሱም፡ አካል ገዝቶ፥ ይኸው፡ በይበልጥ በቤተ ክህነታችን ውስጥ፡ ሕያውነቱ ጸንቶና ተጠብቆ ኖርዋል፤ ይህን ሕያው አቋሙን እንደያዘ፡ ይኸው ዛሬም፡ በህልውናው ቀጥሎበት ይገኛል።

ስለዚህ፡ ፡

፩ኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን መዝሙራችን ውስጥ፡ ...

**"ለዚህ ፊደላችን፡ ለግእዝ ቋንቋችን፤**<br>
ለእውቀት፥ ለጥበብ፥ ለሥልጣኔአችን፤<br>
ለልማት፥ ለዕድገት፥ መሠረት ሕንፃችን፤<br>
በተፈጥሮ ውበት፡ ገነት አገራችን፤<br>
የምንኖርበት፡ የታሪክ ክብራችን፤...

"ካምላክ ያገኘነው፡ ሕገ መንግሥታችን፤<br>
ማንም የማይነጥቀን፡ የሰማይ ወርቃችን፤<br>
የምንጠብቀው፡ ያደራ ውርሳችን፤<br>
ቅዱሱ ኪዳን ነው፡ ሕያዉ ቅርሳችን።" በሚል ቃል

የተገለጸውን እምነታችንን በመከተል፥

፪ኛ፡ "በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን ምክንያት፡ የአገልግሎታችን ቋንቋ፡ **ግእዝ** እና ከእርሱ የተገኘው ኢትዮጵያኛ የተባለው ዐምሓርኛ ሲኾን፡ የጊዜ አቈጣጠሩም፡ በዚሁ ሃይማኖት ላይ የተመሠረተው፡ ሥርዓተ ቀመር ነው።" የሚለውን፡ በእያንዳንዳችን የልብ ጽላት ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተጽፎና በየልቦናችን ማኅደር ውስጥ ተመዝግቦ፡ በአገልግሎት ሥርዓታችን፡ አንቀጽ አሥራ አራት ላይ የሚነበበውን ኪዳናዊ መመሪያ፡ መሠረት በማድረግ፥

፫ኛ፡ የፈጣሪና የቅድስት እናቱ፡ ተቃዋሚ የኾነው የክፋት ኃይል፡ ለእርሱ እንደመሰለው፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን ኢትዮጵያን፡ ደግሞም፡ የእርሷ የኾኑትን ልጆቿንና ዜጎቿን፥ አገልጋዮቿንና ሕዝቧን ብቻ ሳይኾን፡ ስሟ የሚጠራበትን ምድሯንና አገሯን፥ **ግእዝን** እና እርሱን የመሰሉትን ሕያዋን ቅርሶቿን፥ የተፈጥሮ ጸጋዎቿንና ሀብቷን ኹሉ ጭምር፡ በወረራ ይዤ፡ የሚጠፋውን፡ አጠፋለሁ! የሚደመሰሰውን፡ እደመስሳለሁ! የሚበዘበዘውን፡ እበዘብዛለሁ!" ብሎ፡ በጥበቡ፥ በገንዘቡና በኃይሉ ትምክህትና ዕብሪት፥ ድፍረትና ግፍ ተማምኖና ተደላድሎ በሚዝናናበት ጊዜ፡ በእግዚአብሔር፥ የእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር የኾነችው ኢትዮጵያ፥ እርሷም፡ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እርሷና የእርሷ የኾኑት፡ እውነቷም፥ መንግሥቷም፥ ልጆቿም፥ **ግእዝን** እና እርሱን የመሰሉት፡ ሕያዋን ቅርሶቿም፡ መጥፋታቸውና መደምሰሳቸው ቀርቶ፡ መለኮታዊውና ዘለዓለማዊው ካህን ንጉሥ በኾነው፡ በልጇ በወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት፡ እርሷ፡ በመላው ፍጥረተ-ዓለም፥ በምድርም፥ በሰማይም፡ በገናንነት ተንሰራፍታና ሰፍና የኖረች፥ አኹንም የምትገኝ፥ ወደፊትም፡ በዚሁ ህልውናዋ የምትቀጥል መኾኗ፡ እነሆ፡ በይፋ ተገልጦ፡ የምሥራቹ ቀዳሚ መልእክት በተላለፈበትና ቃለ ዐዋዲውም፡ በታወጀበት፡ በቅርቡ ወራት፡ አኹን ደግሞ፡ **የግእዝ** ዕድል ፈንታውና ጽዋ ተርታው መድረሱ ስለተረጋገጠ፡ ይህንኑ አምላካዊ ቸርነትና ጸጋ፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ በአዋጅ ማሳወቅ፡ አስፈላጊ በመኾኑ፡

ከዚህ የሚከተሉትን አንቀጾች የያዘው፡ ይህ ቃለ ዐዋዲ፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ታውጇል።

<u>አንደኛ፡-</u> **ግእዝ፡** የእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር፥ ለእግዚአብሔርም በመኾኑ፡ ቅዱስ ቋንቋ ነው።

<u>ኹለተኛ፡</u> **ግእዝ፡** "አዳማዊ" በተባለበት ስሙ፡ የመጀመሪያው የሰው ልጆች ቋንቋ ነው። እንዲህ በመኾኑ፡ የዓለም ቋንቋዎች ኹሉ እናትና ምንጭ፥ ግንድና መሠረት፥ ቀዳሚና ዘለዓለማዊ ነው።

<u>ሦስተኛ፡</u> **ግእዝ፡** ከአዳምና ከሔዋን ጋር ዐብሮ፡ በእግዚአብሔር ድንቅ ጥበብ የተፈጠረ ስለኾነ፡ የ፯ሺ፭፻፮ የሰባት ሽህ አምስት መቶ ስድስት ዓመታት ዕድሜ ያለው ኾኖ፡ ከኢትዮጵያና ከእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፥ ከቅዱሱ ኪዳናም ጋር በአንድነት የተገኘ ሕያው ጸጋ ነው።

<u>አራተኛ፡</u> ስለዚህ፡ **ግእዝ፡** የኢትዮጵያና የቅዱስ ኪዳኗ፥ የመንግሥቷና የልጆቿ ዘለዓለማዊ ቋንቋ ኾኖ የመኖር ህልውናውን፡ እስከዛሬ አጽንቶ እንደተገኘ ኹሉ፡ ዛሬና ለዘለዓለሙም፡ በዚሁ ሕያውነቱ የሚቀጥል ይኾናል።

__አምስተኛ፡__ **ግእዝ፡** ኢትዮጵያና ልጆቿ፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ እንደቅዱሱ ኪዳን፡ እንዲህ፡ ከእግዚአብሔር ያገኙት ቋንቋቸው ብቻ ሳይኾን፡ የምንነታቸውና የማንነታቸው ልዩ መታወቂያቸውም ስለኾነ፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ፡ ሊጠብቁትና በሕያውነቱ እንዲቀጥል ሊያደርጉ ይገባል።

__ስድስተኛ፡__ ከዚህ የተነሣ፡ ይህ አዋጅ ይፋ እንዲወጣ ከተደረገበት ከዛሬ ጀምሮ፡ **ግእዝ፡** ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ዋናው ቋንቋቸው ይኾናል። ይኸውም፡ ከቸሩ ፈጣሪያቸውና ከቅድስት እናቱ፥ ከቅዱሳኖቻቸውና ከቅዱሳቶቻቸው ጋር በጸሎት የሚገናኙበት፥ እርስ በእርሳቸውም፡ የሚነጋገሩበትና የሚጻጻፉበት፥ አሳባቸውንና እውቀታቸውንም፡ በቃልና በጽሕፈት የሚገልጡበትና የሚለዋወጡበት መደበኛ ቋንቋቸው ይኾናል። ይህም ሲባል፡ ከእርሱ፡ ከግእዝ በሠረፁት፡ ዐምሓርኛንና እርሱን በመሰሉት ተወላጅና ተወራጅ ቋንቋዎች የመጠቀም ምርጫቸውና ነጻነታቸው እንደተጠበቀ ይቀጥላል።

__ሰባተኛ፡__ ይህን የመሰለውን፡ **የግእዝን** ሕያው ማንነት፡ በዚህ ሕያው መልኩና ይዘቱ አጠናክሮና አግዝፎ በማሳየት፡ በእውን ለመፈጸም፡ እያንዳንዱ ኪዳናዊ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኪዳናዊት ኢትዮጵያዊት፡ ይህንኑ **የግእዝ** ቋንቋቸውን፡ ለየራሳቸው ለማወቅና ለሌሎች፥ በተለይም፡ ለልጆቻቸው ለማሳወቅ፡ በየግላቸውና በጋራ፡ በሚቻላቸው ዓቅም፡ ሙሉ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ይህንኑ **የግእዝ** እውቀት፡ **የግእዝ** ምሁራንን በቀጥታ፡ በአካል፥ ወይም በቃል፥ ተገናኝቶ በማነጋገር፥ ወይም፡ በመጻጻፍ፥ ወይም፡ በመጻሕፍት፥ ወይም፡ በዘመናዊው የመገናኛ መስመሮችና በኅዋ አውታሮች በሚተላለፉና በሚሰጡ ትምህርቶች አማካይነት በመከታተል፡ በቀላሉ ማግኘት ይቻላቸዋል።

ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት በኩል እየተዘጋጁ በሚቀርቡ፡ "የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ ትምህርት፡ **በግእዝ** እና በኢትዮጵያኛ (በዐምሓርኛ)" በሚል አርእስት፡ ከመጀመሪያ ደረጃ አንሥቶ፡ በተከታታይ እየታተሙ በሚወጡት መጻሕፍትና በሌሎች ልዩ ልዩ ዝግጅቶችም የመጠቀም ዕድሉ፡ ዓቅም በፈቀደ መጠን፡ በየጊዜው ይቀርባል።

ይህ አዋጅ መውጣቱ፡ ከዚህ በታች የተጠቀሰው፡ እንዲህ የሚለው፡ የስመ ጥሩው፥ የግእዙ አበጋዝና ባለሙያ፡ የኢትዮጵያዊው ምሁር፡ የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ዘቤተ ተክለ ሃይማኖት፡ ትንቢታዊ ተምኔት፡ የመፈጸሙን ዜና ያበሠረን ነውና፡ እጅግ ደስ ብሎን፡ ይህ እንዲኾን፡ ፈቃዱን ለለገሠን ቸር እግዚአብሔር እና ቅድስት እናቱ ለኾነችው ለኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም፡ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

እናንተ እንጂ ናችሁ፡ ያፍሪቃ ራስ ቅል፣
ባለዘውድ ቋንቋ፡ ባለነጻ አክሊል፤
**ግእዝ፡** ዐማርኛም፡ ኹለቱ ቋንቋች፣
ታላቅ፡ ታናሽ አባይ፡ ያፍሪቃ ወንዞች፤
ካፍሪቃ ዐልፈው ተርፈው፡ በባሕር፡ በየብስ፣
ገና ይሰፋሉ፡ እንደግዜር መንፈስ፤
ስላማርኛና **ስለግእዝ** ክብር፣
ዋዜማ ተቊሟል፡ በብዙ አህጉር።"

በመጨረሻ፡ **ስለግእዝ፡** ምናልባት፡ ገና አሟልታችሁና አጣርታችሁ ያልተረዳችሁ ካላችሁ፡ በበለጠ ለመገንዘብ፡ እስካኹን በየመጻሕፍታችን፥ በጎዋ ሰሌዳዎቻችንና መድረኮቻችን ላይ የሠፈሩትን መልእክቶችና መግለጫዎች፥ ማብራሪያዎችና ሓተታዎች መመልከት እንደሚኖርባችሁ እናሳስባችኋለን።

\+ \+ \+

**ተዐውደ፡ በጥቅምት ፳፯ ቀን፥ ፳፻፮ ዓመተ ምሕረት፡ ታወጀ።**

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።